የቆሻሻ መጣያ አንሁን

ቆሻሻ መጣያ አንሁን! አንዳንድ ሰዎች እንደቆሻሻ መጫኛ መኪኖች ናቸው። የያዙትን ቆሻሻ ተሸክመው የሚያራግፉበት ቦታ ይፈልጋሉ። የሚሸከሙትም ስድብ፣ ንዴት፣ ጭንቀት፣ ብልግና፣ ጭቅጭቅ፣ ቁጣ፣ ርግማንና የመሳሰሉትን ነው። ልክ የቆሻሻ መኪና ከየቤቱ ቆሻሻውን እንደሚሰበስበው ሁሉ እነርሱም ከብሶታቸው፣ ከኪሳራቸውና ከደረሰባቸው ችግር ቆሻሻውን ይሰበስቡታል። የቆሻሻ መኪናው ሲሞላ የመጣያ ቦታ እንደሚፈልግ ሁሉ እነርሱም የቆሻሻ መጣያ ስለሚፈልጉ እኛ የቆሻሻ መጣያቸው አንሁን። የሰዎችን ማኅበራዊ ሕይወትና ማኅበራዊ ግንኙነት ያጠኑ ባለሙያዎች እንደሚገልፁት ጥቂት ጠብታ መርዝ፣ የበርሚሉን ዉኃ እንደሚበክለው ሁሉ ጥቂት ሥነምግባር የጎደላቸው ሰዎችም መልካሙን የበርካታ ሰዎች ማኅበራዊ ግንኙነት ሊበክሉ ይችላሉ። መልካም ሰዎች ግን የሚከተሉትን የማኅበራዊ ግንኙነት ምክሮች ይለግሱናል።

የመጀመሪያው ምክራቸው “ባለጌ፣ ሐሳብ አልባና ቁጡ የሆኑ ሰዎች በእናንተ ላይ ቆሻሻቸውን እንዳይጥሉ አጥብቃችሁ ተከላከሉ።” የሚል ነው። በዚህ ምክር መሠረት ሰዎች እንዳይቆጡን፣ እንዳይሰድቡንና እንዳይነተርኩን ማድረግ አንችልም። ነገርግን ከእነርሱ አንደበት የሚወጣው ክፉ ቃል በጆሯችን በኩል ወደልባችን ገብቶ ጎጆ እንዳይሠራ መከላከል እንችላለን።

ሁለተኛው ምክራቸው ደግሞ “ልትቆጣጠሯቸው በምትችሏቸው ነገሮች ላይ አተኩሩ እንጂ በማትቆጣጠሯቸው ክፉ ነገሮች ላይ ጊዜ አታጥፉ” የሚል ነው። “ቁንጫ የጠረጉት ዕለት ባለጌ የመከሩት ዕለት ይብሰዋል” እንደሚባለው ምክርና መልስ ለሁሉ አይሰጥም። ከርከርም ከሁሉ ጋር አይደረግም። ስለዚህ “እዚህ ቦታ ስለናንተ እንዲህ ሲወራ ሰማሁ” የሚሉትን ሁሉ ልትቆጣጠሯቸው ስለማትችሉ አትስሟቸው። ይልቁንስ ራሳችሁን ተቆጣጥራችሁ ስሜታችሁን ገዝታችሁ የራሳችሁን መንገድ ቀይሱ።

ሦስተኛው ምክር “ጋጠወጥነትን በመቀነስና ስልጣኔን በመጨመር ጉልቤዎችን ከነቆሻሻ መኪናቸው ማስቆም ነው።" ‘ለባለጌ ከሣቁለት ለውሻ ከሮጡለት፣ ከባድ አደጋ አለው‘ እንደሚባለው ሰዎች በእናንተ ላይ ጋጠወጥና ያልሰለጠኑ እንዲሆኑ አትፍቀዱላቸው። ይልቁንም መርህአችሁን፣ ጠባያችሁንና መስመራችሁን ግልፅ አድርጉላቸው። ስለዚህ ጋጠወጥነትን በጋጠወጥነት፣ ስድብን በስድብ፣ ክፋትን በክፋት፣ ሳትመልሱ የሰለጠነ፣ ሕጋዊ የሆነና ችግሩን የሚፈታ መንገድ ፈልጉ። ከሁሉም በላይ ምንጊዜም እናንተ ራሳችሁን ብቻ ሁኑ።

አራተኛው ምክር “በጎረቤቶቻችሁ፣ በጓደኞቻችሁ፣ በቤተሰቦቻችሁና በሥራ ባልደረቦቻችሁ ላይ ቆሻሻ ባለመድፋት ጠባያችሁን ግሩ” ይላል። ከቻላችሁ ከአናንተ ቆሻሻ ነገር እንዳይወጣ አድርጉ። በተለይ በተናደዳችሁ ጊዜ ከሰዎች ጋር መከራከርን ተው። ከሰዎች ጋር ለመነጋገሪያ መልካም ጊዜ ምረጡ፣ ስሜት በርዶ አዕምሮ ተገቢ ቦታውን ሲይዝ ተነጋገሩ። የተናደዳችሁበትን ሰው ወዲያው አታግኙ። ስድብ ሰውን ስለማይለውጥ ከስድብ ተቆጥባችሁ ሰዎችን ሊያርሙ የሚችሉና ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችሉ ሌሎች መንገዶችን ለመጠቀም ሞክሩ።”

የመጨረሻው ምክር “በየቀኑ ለመደሰት ሞክሩ፤ የምትወዱትን ለመሥራትና የምትሰሩትን ለመውደድ ተጣጣሩ፣ ተግባራችሁ ሁሉ ለውጥ የሚያመጣ ይሁን” ይላል። በየቀኑ መጠጣት፣ አዲስ ልብስ መልበስና ቀልድ ሲቀልዱ መዋል መደሰት አይደለም። መደሰት ማለት አዲስ ነገር ለመሥራትና ትርጉም ያለው ውሎ ለመዋል ወስኖ መነሳት ነው። ከቻላችሁ የምትወዱትን ሥራ ሥሩ። ካልቻላችሁ የምትሠሩትን ሥራ ውደዱ። ለመጥላት ምክንያት ከምትፈልጉ ለመውደድ ምክንያት ፈልጉ። ደስታ ከለውጥ ይገኛል። ለውጥ እያመጣችሁ በሄዳችሁ ቁጥር ደግሞ ለራሳችሁ ደስታን እየሸመታችሁ ትሄዳላችሁ። (ዳንኤል፣ 2009 ዓ.ም ገጽ 111-121 መጠነኛ ተደርጎ የተወሰደ)